# በፅንፈኛ ኒዩ-ሊበራሎች ውትወታ የምንተወው ልማታዊ አጀንዳ ይኖራልን?

**በላይነህ ተገኝ**

ሀገራዊ ጥቅሞቻችንም ሆኑ ህልውናችን የሚረጋገጡት ህዝቦች በየደረጃቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፈጣን ልማት ዕውን ሲሆን መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። የህዝቦች ተጠቃሚነት ሊረጋገጥ የሚችለው ደግሞ ለተዘረጉና ወደፊትም ለሚዘረጉ ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ አውታሮች የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር የኢንቨስትመንት ፍሰቶችን በትኩረት ማስፋፋት ሲቻል መሆኑ እሙን ነው፡፡

የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችን የደህንነታችን ዋነኛ ስጋት የውስጥ እንጂ የውጭ አለመሆኑን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ የውስጣችን ስጋት ተብለው በሰነዱ ላይ ከተጠቀሱት አንኳር ጉዳዩች ውስጥ ዋነኛው ጠላታችን ድህነት ነው፡፡ ይህ ጠላት በሀገራችን የተንሰራፋ ከሆነ እርስ በርሳችን ተጋጭተን ለከፋ አደጋ እንዳረጋለን፣ ዴሞክራሲ እና መልካም አስተዳደር ጠፍቶም ለችግር መዳረጋችን አይቀርም፡፡

ታዲያ የውስጥ ስጋቶቻችን ማስወገድ የምንችለው በታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊና በድርጅታቸው አማካኝነት የተዘረጋው ልማታዊ መንግስታችን ገቢራዊ በማድረግ ላይ የሚገኘው ውጤታማ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ሂደታቸውን በማስቀጠል በተጨባጭ ስንጠቀምባቸው ነው፡፡ እነዚህን በተግባር ተሞክረው የተረጋገጡ ውጤታማ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ባለፉት ጊዜያት በሚገባ ተጠቅመንባቸዋል። ለዚህም ህያው ምስክር የሚሆነው ላለፉት ዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት በአማካይ አስራ አንድ ከመቶ በማደግ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገባችን ነው፡፡

በሀገራችን እየተመዘገበ ያለው የልማት ውጤት የሁሉም የልማት ውጥኖቻችን ድምር ውጤት ነው፡፡ እንደሚታወቀው መንግስት መላው ህዝባችንን በማስተባበር በመሰረተ- ልማት መስክ እጅግ ግዙፍ ለውጥ ለማምጣት አቅዶ እየሰራባቸው ካሉት ዘርፎች መካከል የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ስራ አንዱ ነው፡፡

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከታዳሽ ምንጮች ውስጥ በለተይም ከግድቦቻችን ከ6 ሺህ እስከ 8 ሺህ ሜጋ ዋት አዲስ ኃይል በማመንጨት በዕቅዱ መጨረሻ ኤሌትሪክ የማመንጨት አቅማችንን በከፍተኛው ዕቅድ ወደ 10 ሺህ ሜጋ ዋት ለማድረስ

ታቅዷል፡፡ አንዳንዶ ወገኖች 'ይህን ያህል ኤሌትሪክ የማመንጨት ኃይል ከየት ሊገኝ ይችላል?' የሚል ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ ጥያቄው ትክክል ቢሆንም ምላሹ ግን ወዲህ ነው።...

..በባሮ ወንዝ ላይ እየተሰራ ያለውና 253 ሜጋ ዋት የሚያመነጨው የገናሌ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ፣ 1870 ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ኃይል የሚያመነጨ የግልገል ግቤ ሶስት ፕሮጀክት እንዲሁም ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት የሚያመነጨው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ለፍፃሜ ሲበቃ ብሎም ከታዳሽ ሃይሎች የሚገኘው ሃይል ድምር ውጤት በአምስት ዓመት ውስጥ የ10 ሺህ ሜጋ ዋት ባለቤት እንድንሆን እንደሚያደርጉን ይታመናል፡፡

የሀገራችን የልማት ፖሊሲ አረንጓዴ ኢኮኖሚን የሚደግፍ ነው፡፡ ይህም ዓለማችንን እንደ ብርድ ልብስ ሸፍኖ ከያዘው የካርቦን ልቀት ነጻ በሆነ የኢኮኖሚ ልማት እንዲመራ የሚያደርግ ነው፡፡ የቅርብ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ሀገራችን እ.ኤ.አ በ2025 የዜሮ ካርቦን ልቀትን ተግባራዊ ለማድረግና የሚሊኒየሙን የልማት ግብ ለማሳካት በእንቅስቃሴ  ላይ ትገኛለች፡፡

ታዳሽ ኃይል እያልን ከምንጠራቸው መካከል የውኃ ሀብታችንን ተጠቅመን በምንገነባቸው ግድቦች አማካኝነት የምናመነጨው የኤሌትሪክ ኃይል ነው፡፡ ሀገራችን የውኃ አቅም ሀብቷ በሚገባ ብትጠቀም 45 ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም እንዳላት በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ይህ የሀገራችን የውኃ ሀብት መጠን በአህጉራችን ከዴሞክራቲክ ኮንጎ ቀጥሎ የሁለተኛነት ደረጃን እንድትይዝ አድርጓታል፡፡

እርግጥ ይህን ዕምቅ ሃብታችንን በመጠቀም ውስጣዊ ችግራችንን መቅረፍ መቻላችን አያጠያይቅም። ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የሚመጣ የደህንነት ስጋትንም በብቃት ልንመክተው እንችላለን። ይኸውም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት ነው፡፡ ምንም እንኳን አፍሪካውያን ድሃ አህጉር እንደ መሆናችን መጠን ኢኮኖሚያችን በትንሽ የንፋስ ሽውታ ሊንገራገጭ የሚችል ቢሆንም፤ ከዚሁ አደጋ በፍጥነት ለመውጣት ዘወትር ከልማታዊ አስተሳሰብ እሳቤ መውጣት የለብንም፡፡

ከዚህ አኳያ የሀገራችን ልማታዊ መንግስትና ህዝባችን በጋራ በመረባረብ የውስጥ ስጋታችን የሆነውን ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የሚያቋርጥ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። ይሁንና የእኛ ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት የማይዋጥላቸው አክራሪ ኒዮ-ሊበራሊስቶች ልማታችንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን እንዲገታ የማይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማይቀነጥሱት ቅጠል እና የማይቆፍሩት ጉድጓድ አለ ለማለት አያስደፍርም።

በተለያዩ ጊዜያት እነዚህ ፅንፈኛ ሊዮ-ሊበራል ኃይሎች እየገነባናቸው ባሉት የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫዎቻችን ላይ የተለያዩ የአሉባልታ ወሬዎችን ሲያናፍሱ ከርመዋል፡፡ እኛም

ለአለባልታዎቻቸው በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረቱ እና አሳማኝ የሆኑ በቂ ምላሽ እየሰጠን የጀመርናቸው የልማት ውጥኖቻችን እየቀጠልን ነው፡፡ በቅርቡም ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የተባለ አክራሪ ኒዩ-ሊበራል ተቋምን በመጥቀስ "ኦል አፍሪካ ዶት ኮም" እና "ዘ ስታር" የተሰኙ ድረ - ገፆች እንደዘገቡት፤ ግልገል ግቤ- ሶስት የኃይል ፕሮጀክት በአካባቢው የሚገኘውን የቱርካና ሃይቅን ወደ አሮጌ ሃይቅነት ያሸጋግረዋል ብለዋል፡፡

ተቋሙ በጥናት አገኘሁት ባለው ሪፖርቱ፤ ፕሮጀክቱ በሃይቁ ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች በጣም አደገኛና በቀጣይ ወደ ነበረበት ለመመለስ አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ሲል አመልክቷል። በዚህም የጊቤ ሦስት የኃይል ፕሮጀክት የኦሞ ወንዝ በዓመት ውስጥ ከሚያፈሰው ውኃ 67 በመቶ እንዳይፈስ እንደሚያደርገውና ወንዙንም ለመስኖ የመጠቀም ዕድልም እንደቀነሰ አትቷል –ይኸው አክራሪ ኒዩ ሊበራል ድርጅት።

ድርጅቱ በዚሁ ዘገባው ሳያበቃም ፕሮጀክቱ በአካባቢው ባሉ ሀገራት የግጭት መንስዔ በመሆኑ በዚሁ ሳቢያ የሚፈጠረው ግጭት ወደማያበራ ደም መፋሰስ ሊከታቸው እንደሚችልም ጠንቁሏል። አያይዞም በፕሮጀክቱ ላይ አፋጣኝና ቀጣይነት ያለው ጣልቃ ገብነት እንዲደረግ የአውሮፓ ህብረትና ዩናይትድ ስቴትስን በመማፀን ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጡትን የበጀት ዕርዳታ እንዲያቆሙ በመጠየቅ የዕድገታችን ጋሬጣ ለመሆንም ተንቀሳቅሷል።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። ይኸውም 'ዕውን በአክራሪ ኒዩ ሊበራሎች ውትወታ የምንተወው ልማት ይኖራልን?' የሚል ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ ልብ ያለው ልብ ይላል። እርሱም ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የተሰኘው አክራሪ ድርጅትም ሆነ ሌሎች የተፈጥሮ ተሚጋችና ተከራካሪ ነን ባዮች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማን መሆናቸውንና ተግባራቸውም ምን እንደሆነ በማጤን፣ በመመርመር አህጉራዊና ሀገራዊ ወገተኝነታችንን ማረጋገጥ የግድ የሚል መሆኑ ነው፡፡

እነዚህ የሰው ልጆች የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ነን ባዮች በሚገርም ሁኔታ ፍጹም የረቀቁ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚጠቀሙ፣ ከተፈጥራዊ አኗኗር ዘይቤ ጋር ፍጹም ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ የሚኖሩ ለመሆናቸው እያየን፣ እየሰማን እና እያነበብን ነው፡፡ ይህ ተግባራቸው ለክቡሩ የሰው ልጅ ስራ ቢሆን በጀ ነበር። ዳሩ ግን ዋነኛ ዓላማቸው በእነርሱ አጠራር የተጋረደችው ወይም የጨለማ አህጉር የሚሏት አፍሪካ እና ህዝቦቿ በማያበራ እልቂት እና ጦርነት አዙሪት ተጠምደው በድህነት እንዲማቅቁ ብሎም በእነሱ በጎ ፍቃድ ብቻ የሚሽከረከሩ ጉስቋሎች እንዲሆኑ ማድረግ የዘውትር ፍላጎታቸው መሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው አፍሪካና ህዝቦቿ ለዘመናት በእነሱ እኩይ ተግባር ሲረገጡ እና በምንም ዓይነት መሰረተ ልማት እንዳይጠቀሙ ተደርገዋል። ታዲያ ይህን "ቴክኒካዊ" ስራቸውን ሲያከናውኑ የቆዩ ጸረ - ህዝብ ኃይሎች መሆናቸውን አፍሪካውያኑ ዛሬ ላይ ተረድተው በአንድነት ስለ ራስ ልማት መዘመራቸውን ተያይዘውታል– ተግባራቸው ገና ከዚህ በላይም ረጅም ሂደት የሚጠይቅ ቢሆንም።

እርግጥ የእነዚህ አክራሪ የኒዮ ሊበራል ኃይሎች ዋነኛ አቀንቃኝ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ከፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለም ሴራቸው ባሻገር፤ አፍሪካውያንን እንደ ብርቅዬ እንስሳ የማየት ፍላጎታቸው ነው ፡፡ በመሆኑም ከእነርሱ አኳያ ሲታይ እዚህ ግባ የማይባል መሰረተ ልማት ባልተዘረጋበት አፍሪካ ላይ የሚነዛው አሉባልታ ወሬ አስገራሚ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እናም በአንድ በኩል ከኒዩሊበራሊዝብ አስተሳሰብ ውጪ ሃገራት ለምን ያድጋሉ ሲሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ በጣም ከስልጣኔ የራቁ ህዝቦቿ ከአስከፊ ድህነት ሳይላቀቁ የበለጸጉ ሀገራት ዜጎች እንደ ብርቅዬ እንስሳ እንዲጎበኟቸውና ለጥናት እና ለምርምር ፍጆታ እንዲውሉ ይሻሉ። ከዚህ በመነሳትም እነዚህ ሃይሎች በስመ ሰብዓዊ መብት ተሚጋችነት ዘግናኝ ኢ -ሰብዓዊ ድርጊት ፈጻሚ መሆናቸው እንገነዘባለን፡፡

እናም ውድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡት የአከራሪ ኒዮ -ሊበራል ሥርዓት ባላባቶች የእኛን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የግድ ተከተሉ ሲሉን 'ወግዱ በእኛው ተጨባጭ ሁኔታ ነው ማደግ ያለብን" ያልን እንደሆነ፣ በእጅ አዙር እንደ ኢንተርናሽናል ሪቨርስ ዓይነት ድርጅቶችና ሌሎች ለሰብዓዊ መብት እንሟገታለን የሚሉ አክራሪዎችን በመላክ ፖለቲካዊ አጀንዳቸውን ለማራመድ  የግድ የሙጥኝ እያሉ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ እስቲ ለማንኛውም አክራሪ ተቋሙ በጊቤ ሶስት ላይ ወዳሚረተው ጉዳይ እናቅና።

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክት የሚያስከትለው ችግር በጣም አሳሳቢ እንደሆነና የኦሞ ወንዝ በዓመት ውስጥ ከሚያፈሰው ውኃ 67 በመቶውን እንዳይፈስ እንደሚያደርግና ወንዙን ለመስኖ የመጠቀም ዕድልንም ይቀንሳል ብሏል፡፡ በመሰረቱ ይህ አሉባልታ በምንም ሳይንሳዊ ትንታኔ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ እንደ ተቋሙ መሠረተ-ቢስ ድምዳሜ የኦሞ ወንዝ ወደ ሃይቁ ጭራሽ አይዘልቅም የሚለው አስተሳሰብ  ፈፅሞ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ሃቁም ወዲህ ነው።…

…የግልገል ጊቤ ሶስት ግድብ መገንባት በየጊዜው በቱርካና ሃይቅ የሚታየውን የውኃ መዋዥቅ ወጥነት እንዲኖረው ከመሆኑ በስተቀር በአካባቢው ሥነ - ምህዳር ላይ አንዳች ዓይነት ተልጽኖ የሚያሳድር አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታም በአካባቢው የሚገኙ ህዝቦች በመስኖ የመጠቀም አቅማቸውን የሚያሳድግ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ እነዚህ የአክራሪ ኒዮ- ሊበራል አቀንቃኝ ድርጅት የግልገል ጊቤ ሶስት ፕሮጀክት በአካባቢው በሚገኙ ህዝቦች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋል በማለት ያንገራጎሩት አስገራሚ ዜማም ተጨባጭነት የለውም፡፡ እውነተኛ ምክንያቱም ከቱርካና ሃይቅና ከገባር ወንዞች ተፋሰስ ጋር ተያይዘው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሆኑ ኬንያዊያን ህዝቦች በልማት እጦት ሳቢያ ኑሯቸውን በአሳዛኝ ሁኔታ የሚገፉ በመሆናቸው ነው፡፡

ለነገሩ ግልገል ጊቤ ሦስት የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የአካባቢውን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚለውጥ በመሆኑ፣ በአካባቢው ያሉት ህዝቦች ወደ ስልጣኔ ጎዳና የሚያራምድ እና ህዝቦች ከስልጣኔ የራቁ አኗኗር ተላቀው የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ የሚያስችል ነው፡፡ እናም ይህ ሁኔታ እንደምን የሀገራቱን ህዝቦች የከፋ እንደሚያደርገው ከፅንፈኞቹ በስተቀር ለማንም ግልፅ አይደለም።

ታዲያ እነዚህ የአክራሪ ኒዩ-ሊበራል አቀንቃኞች ይህን የህዝቦችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ይፈሉጉታል ወይ? ብለን ስንጠይቅ አንድ ሃቅ ፍንትው ብሎ ይታያል። እርሱም በሰብዓዊ መብት ስም እየተንቀሳቀሱ ያሉ እነዚህ የአሉባልታ አራጋቢዎች ይህን መሰሉን የልብወለድ ድርሰት የሚፅፉት የአፍሪካንና የአፍሪካውያን ዕድገት ስለማይፈልጉ ብቻ ነው፡፡

ዳሩ ግን በቱርካና ሃይቅ አካባቢ የሚገኙ ኬንያዎቹ ቱርካናዎችም ሆኑ ኢትዮጵያዊያኑ ኛንጋቶሞችና ሙርሲዎች ከዘላለም የድቅድቅ ጨለማ ኑራቸው ተላቀው የኤሌትሪክ የብርሃን ጸዳል መጎናፀፋቸው አይቀሬ ነው። ከዚሁ ባሻገርም  ከሚዘረጉ በርካታ የመሰረተ- ልማት ፕሮጀክቶች ቁጥር አንድ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

እርግጥ ግልገል ጊቤ ሶስት የኤሌትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ለአካባቢው ህዝቦች ከሚሰጠው ልማታዊ ጠቀሜታ ባሻገር፣ አህጉራዊ ፋይዳው ሲለካም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ እናም ሃቁ የአክራሪ ኒዮ- ሊበራል አፈ- ቀላጤዎች እንደሚሉት ሳይሆን፣ የግድቡ ግንባታ እንኳንስ በቀጣናው ውስጥ ችግር ሊያስከትል ቀርቶ በአህጉር ደረጃ የሚያመጣው መሰረታዊ ለውጥ የላቀ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

አዎ! አፍሪካዊያን በእርስ በርስ ግጭት ለዘመናት የዳከሩት በኢኮኖሚ ባለ መዳበራቸው ምክንያት ነው። ይህም ይህ ነው የሚባል መሰረተ ልማት አጥተው በድህነት ማቅ ውስጥ እንዲማቅቁ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ የትኛውም የአፍሪካ ሀገር በልማት ምክንያት የህዝቦቹ ችግር ሆኖ አያውቅም።... እናም እዚህ ላይ ‘እነዚህ ኃይሎች እነርሱ የገነቧቸው የታዳሽ ኃይል የኤሌትሪክ ማመንጫዎች በአካባቢያቸው ችግር ፈጥራል ወይ’ ብሎ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ሃቁን ገልብጠን ስንመለከተው ከታዳሽ ኃይሎቻቸው በተጨማሪ በየአካባቢያቸው

በዓለማችን ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ የኒውክሌር የኃይል ማመንጫ የሚጠቀሙት እነዚህ አክራሪዎቹ እንጂ አፍሪካ አይደለችም፡፡

እናም የግልገል ጊቤ ሶስት የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት እነርሱ እንደሚሉት የቀጣናው የግጭት መንስኤ ሳይሆን፣ የአፍሪካ ሀገራትን በጋራ ለጋራ ጥቅም የሚያስተሳስር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅም የከባቢው ህዝቦች የትምህርት፣ የንፁህ ውሃና የሌሎች መፀረተ-ልማቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ። በመሆኑም ግድቡ ከዚህ ቀደም ልማት አጥተው በከንቱ ጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ አለመግባባት እና ደም መፋሰስ ይታዩባቸው የነበሩ ህዝቦችን ወደ ተሻለ የመግባባት እና የጋራ ተጠቃሚነት ምዕራፍ የሚያሸጋግራቸው ይሆናል፡፡

እናም ማንም ጤናማ  አስተሳሰብ ያለው ሰውም ሆነ ድርጅት የግድቡ መገንባት የሀገራችን የህዳሴ ጉዞ ሌላኛው ብርሃን ፈንጣቂ መሆኑን ማወቅ ያለበት ይመስለኛል። ከዚህ ባሻገርም ለቀጣናው ሀገሮችና ለአህጉራችን ህዝቦች የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያበረክተው አስተዋፅኦም የላቀ ነው፡፡

በመሆኑም ኢንተርናሽናል ሪቨርስ የተሰኘው ድርጅት ከሳሽ በመሆን ለአውሮፓ ህብረት እና ለአሜሪካ "ግድቡ ችግር ፈጣሪ  በመሆኑ ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን የበጀት ዕርዳታ እንዲያቆሙ" ሲል መጠየቁ ፈገግ የሚያሰኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ድርጅቱ በየራሱን ፖለቲካዊ አጀንዳ ለማራመድ ሲል የሚያካሂደው አሉባልታ "ከባለቤቱ በላይ ያወቀ ...." እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ ነው። እናም በአክራሪ ኒዩ ሊበራል አቀንቃኞች ውትወታ የምንተወው አንዳችም የልማት አጀንዳ የሌለ መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል ባይ ነኝ።

ስለሆነም ከእኛ ከኢትዮጵያውያን አልፎ ወንድም ለሆነው የኬንያ ህዝብ እንዲሁም ለአፍሪካችን የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚሰጠን የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብን አንዱ በአሉባልታ ከሳሽ ሌላኛው ደግሞ ዳኛ በመሆን አክራሪ ሃይሎቹ ያሻቸውን  ቢሉም ዓላማው ግልፅ ስለሆነ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም።

እናም  ዋነኛ የውስጥ ስጋታችን የሆነውን ድህነትን ለመታገል የምናደርገውን ጥረት ለመግታት አሜኬላ እሾህ ለሚሆኑ ሃይሎች የምናውሳቸው ጆሮ አይኖረንም። ፍላጎታቸው እኛ ሳንፈቅድላችሁ ለምን ታድጋላችሁ የሚል በመሆኑ ነው። በመሆኑም ፅንፈኞቹ ድህነታችንን በመቀነስና ታሪክ በማድረግ የህዳሴ ጉዟችንን ለማረጋገጥ ከምናደርገው ሽምጥ ልማታዊ ግልቢያ ወደ ኋላ የምንልበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለን ማወቅ ይኖርባቸዋል ባይ ነኝ፡፡ ቸር እንሰንብት።